# ከቴዎድሮሳዊ ራዕይ ተመዞ የወጣዉ የጋራ ማንነት ላይ የቆመ ሀገራዊ እሴት

በሸንቁጥ አየለ (shenkutayele@yahoo.com)

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ሁለት ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ አንደኛዉ በዕዉቀቱ ስዩም 'ዳግማዊ ቴዎድሮስ የሞራል አርያ ተደርገዉ የሚቆጠሩ አልነበሩም፡፡ ከዘመነኞቻቸዉ ጋር ሲነፃፀሩ ንጉሱ በሞራል ሁዋላቀር ነበሩ' በማለት የሚያራምደዉ አቋዋም እንዲሁም ፕሮፌሰር መስፍን ስልጣን ፤ባህል አገዛዝ ፤ ፖለቲካና ምርጫ በሚለዉ መፅሃፋቸዉ አሁን ያለዉ የፖለቲካችን እሴታዊ መሰረቱ ጉልበት ፤ ዱላና አሳደህ በለዉ የሆነዉ ከእነ አፄ ቴዎድሮስ በወረስነዉ ትዉፊታዊ የባህል አስተሳሰብ ፤ እሴትና የተዛባ ስነ መንግስታዊ እይታ ነዉ ብለዉ ከመቶ ሰማኒያ እስከ መቶ አምሳ አመት በፊት የነበረዉን ያስተሳሰብ ማዕከል በግድ ጎትተዉና አዛምደዉ ያሁኑን ዘመን ፖለቲካ ለመተንተኛ ግብአት አድርገዉ የተጠቀሙበት አካሄድ የተዛባ መሰረት ላይ የቆ መሆኑን ለማሳዬት ነዉ፡፡

በርግጥ ሶስተኛ ወገኖችም አሉ የአፄ ቴዎድሮስንም ሆነ የቀደምት ኢትዮጵያን ማንንት ሁሉ በማቆሸሽ፤ ዉለታ በመካድና በማሳነስ ያሁን ዘመን ትዉልድ የቀደሙ አባቶች እርሾዉን ሁሉ ከልቦናዉ ፍቆ እንዲያጠፉ የሚሰሩ፤ የሚተነትኑ ብሎም የሚተጉ፡፡ ሆኖም ለእነዚህ ለሶስተኛ ወገኖች መልስ መስጠት በራሱ ነዉርም ድካምም ብሎም ሞኝነትም ስለሆነ የእነሱን አስተሳሰብ ለመሞገት ጊዜን ማጥፋት ብዙም ትርፋማ የሚሆን አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ነገሩን የሚያደርጉት ወገንን ለማስተማር ወይም ካለፈዉ ዘመን የዛሬዉ ትዉልድ የተሻላዉን እንዴት ሊወስድ ይችላል ከሚል ህሳቤ ሳይሆን ዋና መንደርደሪያና መስፈንጠሪያ ግባቸዉ የቀደመዉን ኢትዮጵያዊ መሰረት ከመካድና ታሪክ አልቦ ህዝብ ከማድረግ ዉጥንና ግብ ስለሆነ፡፡እነዚህ ሶስተኛ ወገኖች ኢትዮጵጵያ የጋራ ሀገራዊ እሴት የሌላት ባዶና ዝም ብላ እንደማይሰራ የመኪና ክፍሎች የተገጣጠመ አካል ያላት ቀፎ ሆና ትታያቸዋለች፡፡ እንዚህ ሰዎች ስለ ሀገሪቱ ታሪክና ሀገራዊ የጋራ እሴት አዎንታዊ ጭብጥ ይዘዉ ይመጣሉ ብሎ መድከም አላዋቂነት ነዉ፡፡ እነዚህን ሰዎችና ቡድኖች ከፍላጎታቸዉና ከራሳቸዉ ራዕይ ጋር ትቶ አዎንታዊ እይታ ያላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ከታሪክ በምን መልክ ሊማሩ ይችላሉ ብሎ ማንሰላሰሉ ብሎም ከልበ ቅን ኢትዮጵያዉያን ጋር በሃሳብ መከራከር መልካም ነዉ፡፡ ስለሆነም የዚህ ፅሁፍ የሀሳብ ሙግት የእነዚህን የሶስተኛ ወገኖችን አስተሳሰብ ለመሞገት የተዘጋጀ አለመሆኑን ከወዲሁ መግለፁ መልካም ነዉ፡፡

የዚህ ፅሄፉ ዋና አላማ የበእዉቀቱን እና የፕሮፌሰር መስፍንን ሀሳብ መሞገት ነዉ፡፡ ሁለቱ ታዋቂ ኢትዮጵያዉያን (በእዉቀቱ እና ፕሮፌሰር መስፍን ) የአፄ ቴዎድሮስን ሀገራዊ እሴት አዎንታዊ በሆነ መልክ ከመቃኘት ይልቅ አሉታዊ ገፅታዉን አጉልተዉና አግዝፈዉ ለማሳዬት የታከቱትና የደከሙት ከባለፈዉ ኢትዮጵያዊ ታሪካችን ምን ልንማር እንችላለን ከሚል ቅን ብሎም ደፋር ምሁራዊ ስሌት ስለሆነ መጀመሪያ ህዝብን ለማስተማር ፤ የተሰማቸዉን ለማካፈል ብሎም የዛሬይቱን እና የነገይቱን ኢትዮጵያ እሴት ለማነፅ የሚያደርጉትን ትጋት በአክብሮት የዘገብኩት መሆኔን በቅድሚያ ለአንባቢ መግለፅ አለብኝ፡፡ ይህን አቋዋማቸዉን ከልዩ ልዩ ስራቸዉ ማወቅና መገንዘብ ስለሚቻል እነዚህን ሁለት ታዋቂ ሰዎች ልሞግት ስነሳ ሙግቴ የተሳሳተዉን አሳባቸዉን ከማቅናት ፍላጎት ብቻ መሆኑንም መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ ሁለቱም ፀሃፍት ስለአፄ ቴዎድሮስ ያደረጉት ትንታኔ መሰረታዊ እፀፅ ያለበት ብሎም ከንጉስ ነገስቱ ድካምና ጥረት የተወለደዉን ልጅ ከማዬት ይልቅ የእንግዴ ልጁ ላይ ትኩረት ያደረገ ትንታኔ ብሎም ከቴዎድሮሳዊ ራዕይ ተመዞ የወጣዉን የጋራ ማንነት ላይ የቆመዉን ሀገራዊ እሴት ክዶ ለከሃዲያን ግብአት ያቀረበ ሀሳብ በመሆኑ ሀሳባቸዉን በሀሳብ ሙግት ዉድቅ ማድረግ ተገቢም፤ ኢትዮጵያዊም ግዴታም ነዉ፡፡

ሀገር ግንባታን ፈታኝ እና ዉስብስብ የሚያደርጉት ጉዳዮች ተሰፈረዉና ተቆጥረዉ የማያልቁ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን መተንተን እና መዘርዘር ይቻላል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ ፖለቲካ፤ ኢኮኖሚ፤ ማህበራዊ ጉዳዮች፤ ታሪካዊ ዳራዎች፤ የወታደራዊ ቀመርና መሰረቶች፤ የእምነት ጭብጦችና መስተጋብሮች ብሎም ተዛማጅ ዝርዝር ነገሮች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮችና ሀገራዊ ጭብጦች ደግሞ የሚተሳሰሩትና የሚቆላለፉት በጋራ ማንነት ላይ የቆመ ሀገራዊ እሴት ድርና ማገር ሆኖ ሀገራዊ ጉዳዮችን የማዋሃድና የማሳለጥ አቅምና ጉልበት ካለዉ ብቻ ነዉ፡፡ ይሄም ሁኔታ የጋራ ማንነት ላይ የቆመ የጋራ ሀገራዊ እሴት ከሁሉም ጉዳዮች በላይና በላቀ ሁኔታ የሀገር ግንባታ ቁልፍ ጭብጥ ሆኖ እንዲፈረጅ ያደርገዋል፡፡

ሀገራዊ እሴት ተብለዉ ከሚዘረዘሩት ነጥቦች ዉስጥ የሀገር ፍቅር፤ የአንድነት ህሳቤ፤ ለወገን መስዋዕት ለመሆን ቁርጠኝነት፤ በማንትና በሀገራዊ ታሪኮች መመካት/ኢትዮጵያዊ ትምክህት/፤ የስራ ፍቅር ፤ ሀገራዊ ጠላትን ለመበቀልና ለማጥፋት የአቋዋም ቁርጠኝነት፤ የራስን ሀይማኖትና እምነት ለማወቅና ለመጠበቅ ያለ ተነሳሽነት ፤ ሀገራዊ ህግና ስርአትን ለማክበር ያለ ግንዛቤ፤ መሪዎችን ለመከተል ያለ ፈቃደኝነት ፤ መብትን እና ግዴታን አንጥሮ ለማወቅ ያለ ትጋት፤ ለፈጠራና ለለዉጥ ያለ ግንዛቤ እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን ሁሉ አቅፎ የሚይዝና የሚያካትት ነዉ፡፡

ሀገር የሚጠፋዉና የሚከስመዉ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ድቀት፤ ሀገራዊ የፖለቲካ ቀዉስ ወይም ሀገራዊ የህዝብ በደል ሲከሰት አይደለም ፡፡ሀገር የሚጠፋዉና የሚከስመዉ የጋራ ማንነት ላይ የቆመ ሀገራዊ እሴት የከሰመ እንደሆነ ብቻ ነዉ፡፡ እናም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ያለቆመችበት ረዥም ዘመን በታሪክ የተከሰተዉና ከሀገራዊ እሴቶች ይልቅ ወንዘኛ እሴቶች ታላቁን የሀበሻ ሀገር ልቦና ያጠቆረዉና ያኮሰመነዉ ለጥቂት አመታት አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት መዳከም ከጀመረበት ከ 1700 ጀምሮ በተለይም ዘመነ መሳፍንት በገሃድ ከተከሰተበት ከ1760 እስከ 1865 ዓም ለዘለቀ ጊዚያትና ለመቶ ስልሳ አመታት እንጅ፡፡

ለመቶ ስልሳ አመታት የኢትዮጵያዊነት የጋራ ማንነት በወንዛዊ ብጥስጣሽ ማንነት ተተክቶ ሀገራዊ እሴትም በወንዛዊ እሴት የተንበረከከበት ወቅት ኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉዞዋ ተገትቶ በጨለምተኛና አናሳ ህሳቤ ማለትም በጎንደሬነት፤ በበጌምድርነት ፤በጎጃሜነት፤ በሸዌነት፤ በትግሬነት ፤ በወሎዮነት፤በየጁነት፤በአገዉነት ተተክቶና እነዚህም ወንዘኛ እሴቶች እያበቡ የነበሩበት ጥቁር ዘመን ሀገሪቱን አንቆ ዉጦአት በነበረ ዘመን አንድ ከፍ ያለ ብርሃንና ራዕይ እልቡና አዕምሮዉ ዉስጥ የሚንቦገቦግ ዜጋ ከምድሪቱ ተፈጥሮ ይሄን ሙትቻና ወንዘኛ እሴት አዳሽቆ ጥሎ በታላቅ ሀገራዊ እሴት ካልተካዉ በቀር መቼም ለብዙሃኑ ህዝብ ህመምና ሀዘን ከመሆን በቀር ብሎም የመቀጨጭና የባዶነት ቅኔን በህይወቱ ዉስጥ እያንጎላቸ ከመኖር ዉጭ ምን አማራጭ ነበረዉ? በርግጥም ምንም አማራጭ አልነበረዉም፡፡

ሆኖም ሁል ጊዜ የህዝብ ማህፀን ድንቅ ነዉና ከዚህ ሁሉ ህመምና ስቃይ ብሁዋላ አንድ ባለራዕይ በዘመነ መሳፍንት ድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ እንደ አብሪ ኮከብ ተስፈንጥሮ ወጣ፡፡ እንዲህ ሲልም ጥያቄ ጠዬቀ፡- የአባቶቼ ሀገር ለምን እንዲህ ተበጣጠሰ? ህዝቤስ በልዩ ልዩ መሳፍንቶች የተለያዬና ቅጥ ያጣ የአገዛዝ ዘይቤ ለምን ይሰቃያል?ለምንስ በሀይማኖት ግጭት/ በጎሳ ግጭት እንዲሁም እርባና ቢስ በሆኑ በርካት ትርኪምርኪ ጉዳዮችን እና ሽፋኖችን በሚያስነሱ ጉልበተኛ ባላባቶች ይሰያያል? ህዝቤስ በስንቱ እብሪተኛ ግጭቶች ይደቃል? የአባቶቼ ሀገር ድንበሩ የት ድረስ ነዉ? እናም መልሱን ደግሞ እራሱ መለሰ፡፡ እንዲህም አለ- የአባቶቼን ሀገር እኔና ህዝቤ እናቀዋለን፤ እኔ ህዝቤን እመራዋለሁ ፤ የአባቶቼን ሀገር አንድ እንዳላደርግ

ምንም አይነት ሀይል ሊከለክለኝና ሊያቆመኝ አይችልም፡፡ ደግሞም አለ ባለራዕይዉ - ለመቶ ስልሳ አመታት የተበተነዉ ህዝብ የጋራ ሀገራዊ ማንነት ላይ የሚቆም ሀገራዊ እሴት ሊፈጠርለትና ይህም ሀገራዊ እሴት የሚያስተሳስረዉ ታላቅ ህዝብ መፈጠር አለበት፡፡ እዚህ ሀገራዊ መሰረት ላይ መጭዉ ትዉልድ እየገነባና እያሰፋ እስከ ኢየሩሳሌም የምትዘረጋዉን ታላቂቱ ኢትዮጵያን ይፈጥራታልና፡፡

በእዉነቱ እንዲህ አይነት ታላቅ ሀገራዊ ጥያቄን መጠይቅና ይህንንም ታላቅ ሀገራዊ ዕዳ ለመሸከም አንድ ሰዉ መጀመሪያ እጅግ ባለራዕይና ወኔያም መሆን አለበት፡፡ ምናልባትም ይህ አይነቱ ሰዉ እጅግ ከፍ ያለ ራዕይና ወኔ ባይኖረዉ እንኳዋን ምናምንቴ ሰዉ ሊሆን ፈፅሞ አይችልም፡፡ወይም ደግሞ በእዉቀቱ ስዩም ሳያፍርና የታላቁ ንጉሰ ነገስትን ዉለታ በእግሩ ረጋግጦ ጥሎ እንደ ፈረደዉ በዚያ ዘመን ከነበረዉ ማህበረሰብ ያነሰ ሞራል ያለዉ ሰዉ ሊሆን አይችልም፡፡ ምናምንቴ ሰዉ እንዲህ አይነት ከባድ ጉዳዮችን ሊነካካ ቀርቶ ሊያስብ አይችልም/አይፈልግም፡፡ በሁለተኛ ደረጃም ለመቶ ሰድሳ አመታት ሀገራዊ እሴቱ ላሽቆና ዳሽቆ ከሀገራዊ እሴት ይልቅ ወንዘኛ እሴት በገነነበት ወቅት ከዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍል ተወልዶ ከትንሹና ከምናምንቴዉ እሴት ይልቅ ከፍ ያለዉን ሀገራዊ እሴት መርምሮ ማግኘት ይህንንም ለህዝብ አንድነትና የጋራ አብሮነት ለማዋል ቆርጦ መነሳት ከተራ ሰዉነት ከፍ ያለ ሰብዕናና የአእምሮ ይዘት ብሎም የሞራል ልዕልና ይጠይቃል፡፡

ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ አንዲት ኢትዮጵያን መልሰዉ ለማዋሃድ ሲነሱ ከገጠማቸዉ መራራ ችግር ዉስጥ የህዝብ ስርአት አልበኝነት እንደነበር ለእንግሊዞች በጻፉት ደብዳቤ ላይ - እናንት ታላቅ የሆናችሁት ስርአት ባለዉ ህዝብ ነዉ እኔ ግን ያለኝ ስርአት ያልገባ ማህበረሰብ ስለሆነ እንደ እናንተ ታላቅ ሀገር ሊኖረኝ አልቻለም ሲሉ ደጋግመዉ ገልፀዋል፡፡ የሀበሻ ሀገር ገና ስለ ስርዓት እና ስርአት ስለ ገባ ማህበረሰብ ባልባነነ ዘመን እንዲህ ባለ ጥልቅ ጉዳዮች ሲብከነከን የኖረን ሰዉ በአሁን ዘመን ላይ ቆሞ በዘመኑ ከነበረዉ ማህበረሰብ ያነሰ የሞራል ልዕልና ያለዉ ሰዉ ነበር ብሎ መፈረጅ በእዉነቱ ያስገርማል፡፡ እዉነታዉ ግን አፄ ቴዎድሮስ ከፍ ያለ አዕምሮ እና ራዕይ ያለዉ ሰብዕናን ተላብሶ ታላቁን ህዝብ የታላቅ ሀገር ባለቤት ሊያደርጉት ወገባቸዉን ሸብ አድርገዉ ተራራማዉን ሀገር ሁሉ በሀሳብም በእግርም ማስነዉበታል፡፡ ኢትዮጰያን መልሶ ለማዋሃድ፤ ስርአት የገባ ሀገር ለመፍጠር ብሎም የወንዘኛ እሴትን ደምስሶ በታላቅ ሀገራዊ ማንነት ለመገንባት ታላቁ የኢትዮጵያ ባለዉለታ ማስነዋል፤ ደክመዋል ብሎም እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሻቸዉ ድረስ ክቡር ህይወታቸዉን ለተከበረ ራዕይ ሰዉተዋል፡፡

ሌላዉ ቀርቶ ዛሬ የዲሞክራሲ ህሳቤ ቢያንስ በተማረዉ ህዝብ ዉስጥ ግንዛቤ አግኝቶአል በሚባልበት ዘመን ዉስጥ እንኳዋን ያሉ ፖለቲከኞች ዲሞክራሲን ያራምዳል የሚባል ፓርቲ ብጤ ከመሰረቱ ብሁዋላ ወይም ማህበር ብጤ ካቋዋቋዋሙ ብሁዋላ አንድ ትርጉም ያለዉ ፋይዳ ሳይፈይዱ አላግባብ ጎጃሜዎች በዝተዉና በርክተዉ አመራሩን ያዙት ፤ ሰሜን ሸዋዎች ተጠራርተዉ አመራሩን ስለያዙት የሸዋን የበላይነት ሊመልሱ ነዉ፤ ወሎዎች በሙሉ አመራሩን ነጠቁን፤ እኛ ጎንደሬዎች ከጎጃሜዎች ጋር አብረን ተጣጥመን ልንሰራ አንችልም በሚሉ ሰንካላና ከዘመነ መሳፍንት በተወረሱ አራሙቻ እሴቶች ታጥረዉ አገራዊ አንድነት እንሰብካለን ሲሉ በወንኛ አስተሳብ የተጠረዙና ያንኑ ፓርቲ/ማህበር ብለዉ ያቋዋቋዋሙትን የሚበትኑ ሰዎች በአሁን ሰአት መገኘታቸዉ የዘመነ መሳፍንት መርዛማ ሀገራዊ እርሾ ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር ለማገናዘቢያነት ከበቂ በላይ ነዉ፡፡ ይህን ሁኔታ ስናይና ስንገመግም ታላቁ ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸዉ ከነበሩት ሰዎችና መሳፍንት አይደለም አሁን ዘመን ላይ ካሉ ወንዘኛ እሴት አራማጅ ፖለቲከኞች እንኳዋን የላቀ የሞራል መሰረት ያላቸዉ ሀገራዊ አባት መሆናቸዉን በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ ይህን መካድ ለአንድ ኢትዮጵዊ ነዉር ብቻ ሳይሆን አንድ ያልጠራ አስተሳሰብ በልቦናዉ ዉስጥ ተሸጦ ይገኛልና ይሄን አስተሳሰብ ደጋግሞ መፈተሸና ወደ ትክክለኛዉ መስመር መመለስ አዋቂነት ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ አጼ ቴዎድሮስ በተነሱበት ወቅትም ሆነ ከእርሳቸዉ ቀደም ብሎ ሲቀጥልም አሁን ድረስ ባሉት ዘመናት ኢትዮጵያ ለቁጥር በሚያዳግቱ ጠላቶች የተከበበች ሀገር፤ የጠላቶቹዋ ብዛት ለመተንተን እንኳዋን ናላ የሚያዞር መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ የጠላቶቹዋ ፍላጎትም እንደዚሁ ስብጥርና ዝብርቅር በመሆኑ ወጥ ስትራቴጅ ሊቀረፅለት የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ይህን የኢትዮጵያን ጠላቶች ስፋትና ጥልቀት ጉዳይ ግሩም በሆነ መልክ አፍታትተዉና አብራርተዉ በታላቅ ምሁራዊ ትንታኔ አቅርበዉታል፡፡ ለዚህ ስራቸዉ ያለኝን ከፍ ያለ አክብሮትም በዚህ አጋጣሚ መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡

ከሩቅና ከቅርብ ጠላት ዙሪያዉን የወረረዉ ሀገርን ፤ ስርአት ያልገባ ህዝብን ፤ በጉልብታቸዉ የሚታመኑ እብሪተኛ መሳፍንት ሀገሩን በወንዝ ከልለዉ የተከፋፈሉት ህዝብን፤ በወንዘኛ እሴት ልቦናዉ የተቀነበበ ህዝብን ብሎም አንድነቱ ለመቶ ስድሳ አመታት የተበተነበት ህዝብን አንድ አድርጎና ሰብስቦ ለመምራት መነሳት ምንኛ መከራና እዳ ነዉ?እንዲህ አይነቱን ተስፋ አስቀራጭ ሁኔታ ለመጋፈጥስ የሚቆርጥና የሚነሳስ ቴዎድሮሳዊ ራዕይን ካነገበ ሀይል ዉጭ ማን ሊሆን ይችላል? ለምሆኑ የቴዎድሮሳዊ ራዕይ ምንድን ነዉ? ከዚህ ቴዎድሮሳዊ ራዕይ የተወለደዉስ ታላቅ ሀገራዊ እሴት ምንድን ነዉ? ቴዎድሮሳዊ ራዕይ ተጠቅልሎ ወደ መሬት ሲወርድ አንዲት ኢትዮጵያ የሚለዉ ጭብጥ ነዉ፡፡ ከዚህ ራዕይም ነጥሮ የሚወጣዉ ሀገራዊ እሴት ለአንድነት መሰዋዕት ለመሆን ፍፁም ፈቃደኛ የመሆን ስነልቦናን የተላበሰዉ ኢትዮጵያዊ ተክለ ሰብዕና ነዉ፡፡ በወንዘኛ እሴት ታጥሮ ከመቀመጥና የስልጣን መሰረትን በወንዘኛ እሴት ወርድና ስፋት ከማጠር ይልቅ ታላቂቱን ኢትዮጵያን ለመፍጠር ያላሰለሰ ፤ያልተቋዋረጠ እና እልህ አስጨራሽ ትግልን ማድረግ ቅዱስና ብሩክ የሕይወት ግብ ነዉ የሚሉት ሀገራዊ እሴቶች በኢትዮጵያ ማህበረሰብ አዕምሮ መፍሰስና መመላለስ የጀመሩት አፄ ቴዎድሮስ ሀሳቡን ተግባራዊ ካደረጉት ብሁዋላ ነበር፡፡ ለአንድ መቶ ስልሳ አመታት ያህል ድምጥማጡ ጠፍቶ የነበረዉን የጥንታዊት ኢትዮጵያዊነት ህሳቤን ከተቀበረበት ቆፍረዉ ያወጡት አፄ ቴዎድሮስ የመሰረቱት እዉነትም የተመኙት ራዕይ ግቡን የመታዉ በኢትዮጵያዊዉ ማህበረሰብ ዉስጥ በዘሩት ሀገራዊ እሴት ነዉ፡፡

የቴዎድሮስ ራዕይን ቀጣይነት አስፍተዉና አምልተዉ እዉን ያደረጉት ታላቁ አፄ ሚኒሊክ እራሱ ተክለ ሰብዕናቸዉ የተቀረፀዉና የኢትዮጵያዊነት እሴታቸዉ የተጠነጠነዉ በአፄ ቴዎድሮስ የራዕይ ዉጥን እና ስሌት ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ አጤ ቴዎድሮስ ያባቶቼ አገር ብለዉ በራዕያቸዉ ዉስጥ ያካተቱት አፄ ምኒሊክ በሂደት ያዋሃዱትን መላዉን ኢትዮጵያን ብሁዋላም በንጉሰ ነገስት አፄ ሀይለስላሴ የተቀላቀለችዉን ኤርትራን ጨምሮ ከቀይ ባህር ማዶም እየሩሳሌምን ጭምር ነበር፡፡ እንዲህ ባለታላቅ ሀሳብና ባለታላቅ ራዕይ የሆኑትን ብሎም ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅና ሰፊ ሀገርን ሊያበረክቱ የማሰኑትን ንጉሰ ነገስት ዛሬ አንድ ገበሬ እንኩዋን ካንዱ ክልል ወደ ሌላዉ ክልል ሄዶ ጠንክሮ ስለሰራ ከበርቴ ሆነ/ዛፍ ጨፈጨፈ/ ተብሎና ሀብቱ ተነጥቆ የሚባረርበት ሀገርና ሀገራዊ እሴት የዋጠዉ ሀገር ዉስጥ የሚኖር ፀሃፊ በሙሉ አፉ አጤ ቴዎድሮስን በዚያ ዘመን ከነበረዉ ማህበረስብ የላቀ የሞራል የበላይነት አልነበራቸዉም ብሎ ማለት አለማፈር ነዉ፡፡ ያሉበትንም ሁኔታ በዉል አለመረዳት ነዉ፡፡ ለምሆኑ እኔን ጨምሮ በእዉቀቱስ ፤ ፕሮፌሰር መስፍንስ በጠቅላላዉ የዚህ ትዉልድ አባልስ አፄ ቴዎድሮስ የነበራቸዉን ያህልና እስከ እየሩሳሌም የምትዘረጋ ኢትዮጵያን በልቡ ያነገበ ታላቅና ሰፊ ሀገራዊ ራዕይ አለን? ለዚህ ራዕይስ ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ የደከሙትን ያህል አንድ መቶኛዉን ያህል ደክመናል? ወይስ ለመድከም ፈቃደኛ ነን? ደግሞስ የአሁኑን ዘመን የፖለቲካ ጭብጥ ለመተንተን ወደ ታላቁ ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ እሴት ላይ መንጠልጠል

አግባብ ነዉ? እነዚህን ነገሮች ለመተንተን መነሳት በራሱ ትልቅ እርምጃ ቢሆንም በትንታኔ ሂደት ዉስጥ ግን ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ መልካም ነዉ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ራዕያቸዉን ወደ ተግባር የለወጡት ምን አይነት ስልትና ስተራቴጅ ተጠቅመዉ ነበር የሚለዉን ቁንጥል ነገር ብቻ ነጥሎ በማዉጣት አፄ ቴዎድሮስን በስትራቴጅያቸዉና ስልታቸዉ ብቻ በማጠር የቴዎድሮስ ሰብዕናን ለመገምገም መነሳት አቢይ ስህተት አለበት፡፡አፄ ቴዎድሮስን ከራዕያቸዉ በመነጠልና የተከተሉትን ስትራቴጅ /ስልት ብቻ በማጣቀስ ቴዎድሮስን ጨካኝ ነበሩ ለማለት መንደርደር በምልዐት ያልተቃኘ ትንታኔ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለምን አፄ ቴዎድሮስ ያን አይነት ስልትና አስትራቴጅ ተከተሉ የሚለዉን ጭብጥ በዚያን ወቅት ከነበረዉ መሰረታዊ ኩነት ጋር ሳያገናዝቡ ሁኔታዉን በዘፈቀዳዊ ተምኔት ወደዚህ ዘመን ጎቶ በማምጣት ብቻ አጤ ቴዎድሮስ ጨካኝ እርምጃዎችና አስገዳጅ ሁኔታዎች ይወደስዱ ስለነበረ ይሄዉ እሳቸዉ ያወረሱን አካሄድ ለዛሬም ትዉልድ እሴቱ ሆነ ማለት አስቂኝ ትንታኔም ባይሆን በደንብ ያልተገራ ትንታኔ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ባለራዕይዉ አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ሲነሱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ገዥ ነበሩ

1. ሀገሪቱ ተበጣጥሳ ማዕከላዊነት አጥታ ማህበረሰቡ በወንዘኛ እሴቶች ተጠርንፎ በተለይም የዬወንዙ መሳፍንት ወንዘኛ እሴታቸዉን መሰረት አድርገዉ ህዝቡን በጎሳ እያጋጩ፣ በሀይማኖት እያፋተጉ ለራሳቸዉ የተመቸ የዘረፋ ስልትን በመቀይስ ህዝቡን ሲበዘብዙ ነበር ፡፡
2. ሥርአት አልበኝነት በወንዘኛ መሳፍንቶች እንደ ስርዓት ተወስዶ ህዝቡ ራሱ ስርዓት ያልገባ ህዝብ ሆኖ ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ማሳያዉ ማንም ጉልበትኝነትና ማን አለብንነት ከተሰማዉ በህዝቡ ላይ ለመንገስና የበላይ ለመሆን ያለስርዓት የሚራኮትበት ወንዘኛ መሳፍንት እንደ አሸን ለመፍላት አንዳችም የሚገታቸዉ ሁኔታ ያልነበረበት ሁኔታ ነበር
3. እንደማንኛዉም ፊዉዳላዊ ስርአት ጦርና ጦርነት ዋነኛዉ የፖለቲካ ግብ ማራመጃ መሳሪያ ከመሆኑም በላይ አገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት አጥታ ስለነበረ ጉልበተኞቹ መሳፍንት እርስ በእርስ የማይደማመጡ፣ በሀይልና በጉልበት ስሌት ብቻ የሚያምኑ መቻቻል ምክርና ለጋራ ታላቅ ሀገር በጋራ መስራት የሚለዉ ህሳቤ መዘባበቻ የሆነበት ዘመን ነበር፡፡
4. እነዚህ ወንዘኛ ጉልበተኞች የቤተክርስቲያን መሪዎችን በማስገደድም ፤ በማስፈራራትም ፤ ጥቅማጥቅም በማላስም፣ ይህ ሁሉ ካልሰራ ደግሞ ሀሰተኛ የሀይማኖት አባቶችን እራሳቸዉ እየሰዬሙና እያወጡ ህዝቡን በእምነቱ በኩል ለማዘዝ የራሳቸዉን ቀመር በመስራታቸዉ ቤተክርስቲያንን ሳይቀር አስገድደዉ የራሳቸዉ አገልጋይ አድርገዉ የያዙበትም ሁኔታ ነበር
5. ማህበረሰቡ ከብዙ አቅጣጫ በሚደርስበት የጉልበተኞች ምት የድንጉጥነት ባህሪ ከመላበሱም በተጨማሪ በብዙ ኩነቶች የተወናበደበት ሁኔታ ተፈጥሮበት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ባለ ራዕይ መሪዎችን ከምናምንቴ መሪዎች ለመለዬት ብሎም ከትክክለኛዉ ወገን ትክክለኛዉን መመሪያ ለመቀበል መወናበድ የነበረበት ሁኔታ ነበር፡፡
6. ከኢትዮጵዊነት እሴት ይልቅ ወንዘኛ እሴት የበላይነቱን የጨበጠበት እና የቡድኖች ስብስብ መገበርም ሆነ የማስገበር ቀመር በዚሁ ወንዘኛ እሴት ማጠንጠኛ ላይ ተመርኩዞ የሚከወንበት ሁኔታ ነበር፡፡ በመሆኑም ጎንደሬዉ ቴዎድሮስ ሊነግስብን ነዉ ብለዉ ሸዌዎች፣ ጎጃሜዎች፣ ወሎዎች ፤ ትግሬዎች በየፊናቸዉ ይህን ሰዉ ለማጥፋት ሳይታክቱ ሳይደክሙና ሳያፍሩ ነገር የሚያጠነጥኑበት ብሎም ጦር የሚሰብቁበት ሁኔታ ዉስጥ ነበሩ፡፡ ሰዎች የሚለኩት በችሎታቸዉ ወይም በጀግንነታቸዉ ሳይሆን ባላቸዉ ወንዘኛ ቀረቤታ ነበር፡፡ በአሁን ዘመን የጎሳ ፓርቲ መስርተዉ በጎሳ ቀመር ከሚሻኮቱት ፖለቲከኞች በባሰ ሁኔታ ወንዘኞቹ የዘመነ መሳፍንት ጉልቤዎችም ኢትዮጵያዊነት የሚለዉ የጋራ እሴት የሚመራቸዉ/የማይዋጥላቸዉ/ ሆኖም የወንዛቸዉ ጉዳይ የሚያማልላቸዉ እይታቸዉ የተቀነበበና የመከነበት ሁኔታ ነበር፡፡

እንግዲህ ባለራይዕዉ ቴዎድሮስ በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ነበር ታላቁን የአንዲት ኢትዮጵያ ራዕያቸዉን ወደ ተግባር መለወጥ የነበረባቸዉ፡፡ እና ምን ምን አማራጭ ስትራቴጅ ነበራቸዉ? እንደራደርና ተባብረን አንዲት ኢትዮጵያን እንፍጠራት ብሎ ወንዘኛ መሳፍንትን ማግባባት? ይህ ሊሆን አይችልም ነበር፡፡ በሁለት ምክንያት፡፡ አንደኛ ወንዘኞቹ መሳፍንቶች ከዱላ ከጦርና ከድብድብ በቀር ልባቸዉን ሊያንበረክከዉ የሚችል ምንም አይነት ምድራዊ ሀይል የለም ብለዉ የሚያምኑ ነበሩ፡፡ ሁለተኛም አጤ ቴዎድሮስ የወጡበትን ማህበራዊ ስር /የኮሶ ሻጭ ልጅ እያሉ/ እያጣቀሱ ከቴዎድሮስ ጋር በታላቅ ሀገራዊ ጉዳይ ሊመክሩ ይቅርና የአንድ አዉራጃ መሪ እንኳዋን ሊሆኑ አይገባም የሚሉዋቸዉ መሳፍንት ነበሩና፡፡ይህ ፖለቲካዊ አቋዋም በአሁን ዘመን የመስፈሪያ ወጭትና ቁና ላይ ተቀምጦ ከተንጠረጠረ ለዚህኛዉ ዘመን ሰዉ የሚያስተላልፍለት መልዕክት የመሳፍንቱን ባዶ ትምክህት ነዉ፡፡ ሆኖም በዚያኛዉ ዘመን ዉስጥ ሲለካና ሲሰፈር ግን ትርጉሙ ሰፊ የሆነ የፖለቲካ ጨዋታን ተንተርሶ የቆመ ጭብጥ ነዉ፡፡ በመሆኑም አጤ ቴዎድሮስ ይጫዎቱበት የነበረዉ የፖለቲካ መድረክ ባህሪዉ በራሱ ሁኔታ ዉስጥ እጅግ ዉስብስብና አስቸጋሪ ነበር፡፡ በምንም መልኩ ወደዚህኛዉ ዘመን ተጎትቶ የሚመጣ ተመሳሳይ ኩነት/ጭብጥ አይገኝለትም ተብሎ ባይደመደምም የዚያዉ ዘመንን ጭብጥ ወደዚህኛዉ ዘመን ጎትቶ ለማምጣት መሞከር ግን ከአዎንታዊ ገፅታዉ አሉታዊ ግብአትነቱ ያይላል፡፡

ፖለቲካ በአንድ ዘመን በሚፈጠር የፖለቲካ ማህበረሰብ አስተሳሰብና ስርአት ለመመራትና ለመተዳደር የሚከተለዉ የየዘመኑ ህግና ስርአትን መሰረት አድርጎ የሚዘወርበት ርዕዮት አለም መነሻና መድረሻዉ በዋናነት ዘመኑ እራሱ መሆኑ እሙን እና ቅቡል ሆኖ ሳለ ፕሮፌሰር መስፍን ይህን የረሱ እስኪመስል ወደ ቀደሙ ዘመናት ተሸግረዉ ያለ ጥልቅና ሰፊ ትንታኔ፣ የአሁኑ ዘመን ከዚያኛዉ ዘመን ጋር አንድ/ልዩ የሚያደርጉት አንኩዋሮችን/variables/ ነቅሰዉ ሳያወጡ ያ ዘመን እንዲህ ስለነበረ ዛሬ ባለንዉ ማህበረሰቦች ላይ እንዲህ አይነት ባህላዊ ጫና አመጣብን ብለዉ ሊነግሩን ይነሳሉ፡፡

በመላዉ አለም ከሁለት መቶ አመት በፊት የነበረዉ የስልጣን መወጣጫ ህሳቤና ስልት በጦርነት ጠላትን ማንበርከክ ብቻ እንደነበረ በመዘንጋትና በመላዉ አዉሮፓና ሌሎች አካባቢዎች እንደነ ናፖሊዮን ፣ ቢስማርክ የመሳሰሉ ጦረኛ መሪዎች ጠላቶቻቸዉን በመደምሰስ ሀገራቸዉን ያዋሃዱት በጠነከረዉ ወታደራዊ ስርአታቸዉና በመራራዉ ቅጣታቸዉ መሆኑን ሳያገናዝቡ የአጼ ቴዎድሮስን ጨካኝነት ለማጉላት ሲሉ የዚህን እጅ ቆረጠ የእነዚያን አንገት ቀላ ይሄም የሚያሳዬዉ የኢትዮጵያ ባህላዊ የስልጣን መሰረቱ ሀይልና ዱላ ነዉ ሲሉ ፈጣን ድምዳሜ ላይ በመድረስ የታሪካችንን ወሰንና ዳር እጥርጥር የሚያደርጉልን ፀሃፍትና ተንታኞች ትንታኔ ስልት ደግመዉ ማጤን አለባቸዉ፡፡ ከነዚህ ፀሀፍት ዉስጥ አንዱ ደግሞ በምሁራዊ ትንታኔዎቻቸዉ የብዙዎቻችንን ህሳቤ የሞረዱን ፕሮፌሰር መስፍን መሆናቸዉ አስገራሚ ነዉ፡፡ ለፕሮፌሰር መስፍን የሚሰነዘረዉ አንድ ጥያቄ ከሁለት መቶና ከመቶ አምሳ አመት በፊት የሆኑ ኩነቶች ለዚህ ዘመን ፖለቲካዊ የባህል ጭብጥ ከሆኑ ታዲያ ቢስማርክ የመራት ሀገር፣ ናፖሊዮን የመራት ሀገር እንዴት ዛሬ ዲሞክራሲን ማስፈን ቻሉ ? መልሱ ግልፅ ነዉ የዚህን ትዉልድ ዉድቀት እዚሁ እትዉልዱ አፍንጫ ስር ከመፈለግ ይልቅ እሩቅ መባዘን የፈጠረዉ መደናገር ነዉ፡፡

ለምሆኑ በዚያን ዘመን አጼ ቴዎድሮስ ከሸዋ ጦረኞች ጋር ፣ ከጎጃም ጦረኞች ጋር ፣ ከወሎ ጦረኞች ጋር ፣ ከትግራይ ጦረኞች ጋር ተደራደረዉ የኢትዮጵያን አንድነት ማምጣት ይችሉ ነበር? እነዚህ ፀሀፍት እንዲህ አስበዉ ከሆነ የፊዉዳሎችን የጦረኝነት እና የሀይለኝነት ባህሪ አሁን አለም

ከደረሰበት የዲሞክራሲ ህሳቤ ጋራ የማቀላቀል ስህተት እየሰሩ ነዉ ማለት ነዉ። ነዉ ወይስ አፄ ቴዎድሮስ በዘመኑ የማይታወቀዉን የዲሞክራሲዊ ስርአት ባለመከተላቸዉ በአሁን ዘመን ዲሞክራሲ በራበዉ ትዉልድ ሊወቀሱ ይገባቸዋል ወይ?

አጼ ቴዎድሮስ ቆራጥና የተዋጣላቸዉ ጀግና ነበሩ እንጅ ጨካኝ ንጉስ አልነበሩም። ለዚህም የታሪክ ማስረጃን አንድ ሁለት ተብሎ ሊነቀስ ይችላል፡፡ አንደኛ ቴዎድሮስ ጦርነት ገጥመዉ ካሸነፉ ብኋላ እና አንድ አካባቢ ለእሳቸዉ መገበሩን ካረጋገጡ የንጉሶቹን ዘሮች አያጠፉም፣ አካባቢዉንም አያጠፉም ነበር።የቴዎድሮስ ብቸኛ ራዕይ የተበተነዉ ህዝባቸዉ በሀይል በአንድ እንዲሰበሰብ ብቻ ነበር። ይህ የሃይል ህሳቤ ደግሞ በዘመኑ የነበረ የመላዉ አለም መሪዎች ፍቱን አማራጭ መሆኑ ከላይ ተብራርቶአል። ማረጋገጫ የሚል ካለ የሸዋዉ ምኒሊክን ልጃቸዉ አድርገዉ ይዘዉ ሄዱ ፤ የወሎ ገዥዎችን ካስገበሩ ብኋላ አንድም ሳይነኩ ተቀብለዋቸዋል። በርካታ የቴዎድሮስ ተቀናቃኞች የቴዎድሮስን የበላይነት አምነዉ ለአጼ ቴዎድሮስ ከገበሩና እጅ ከሰጡ አጼ ቴዎድሮስ የሚገባቸዉን ክብር ሰጥተዉና አሞላቀዉ ያኖሯቸዉ ነበር። ቴዎድሮስ ደግ ሩህሩህ የነበሩት ለመላዉ ህዝባቸዉ ጭምር ስለነበረ የሚያወጡዋቸዉ አዋጆችና የመተዳደሪያ ህጎች በተቻለ መጠን ህዝቡን እንዳይበድሉባቸዉ ይጠነቀቁ ነበር። ይህ ማለት ግን የሚወጡ አዋጆችና ህጎች አሁን አለም ከደረሰበት የህግ ህሳቤ ጋር ተወዳዳሪ ነበሩ ማለት አይደለም፡፡

ሆኖም የቴዎድሮስን ጀግንነት የተጠራጠሩና ያንገራገሩ ወገኖች/በተለይም ኮሶ ሳጭ በማለት ሊያኮሰምኑዋቸዉ የሞከሩ ወገኖች / የሚቀጡት ቅጣት መራራና የማያዳግም ነበር። እንግዲህ አንዳንድ ፀሀፍት የቴዎድሮስን አስተዋፅኦ በደንብ ሳያብሰለስሉ የቴዎድሮስን ምህረት ሳሆን ቅጣት መዘዉ ያወጣሉ፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነንም ሸዋና ጎጃም አልገብር ብለዉ ለሁለተኛ ጊዜ በድጋሚ ከቴዎድሮስ ጋር ጦርነት ዉስጥ የገቡ ጊዜ የተቀጡት ቅጥ መራራ መሆኑ ነዉ። በዚህ ዘመን ላይ አንድ ጸሃፊ ተነስቶ የቅጣቱን መራራነት ጠቅሶ የቴዎድሮስን ጨካኝነት ለማሳዬት ከሞከረ ይሄ ጸሃፊ የዚያ ዘመን የነበረዉ ማህበራዊ ዉቅረትና አጠቃላይ የስልጣን ስነልቦናዊ መሰረት አልገባዉም ማለት ነዉ። ጦርነትና ሀይል ብቸኛዉ የስልጣን መሰረት መሆንኑ ተቀናቃኞቹ ጦረኞችም መራራ ተዋጊ እንደነበሩና ቢሳካላቸዉ ደግሞ ተመሳሳይ እርምጃ በተቀናቃኛቸዉ ላይ ወስደዉ ተቀናቃኛቸዉን ከመዋጥ እንደማይመለሱ አልገባዉም ማለት ነዉ። ደግሞም ይሄ እዉነትና አጠቃላይ የስልጣን መወጣጫ ስልት በኢትዮጵያ የነበሩ ጦረኞች ጋር ብቻ ይሰራ የነበረ ሳይሆን በመላዉ አለም ይሰራበት የነበረ የፊዉዳል ጦረኞች  ስልት ነበር።

የዚያ ዘመን ታሪክ፣ የባህል እሴትና የስልጣን መሰረት ዋና ስልቱና ቅኝቱ በጦርነት ማሸነፍ ነበርና አጼ ቴዎድሮስ ከዚህ የተለዬ ነገር አላደረጉም ነበር። አጼ ቴዎድሮስ ከዘመነ መሳፍንት ጀምረዉ የኢትዮጵያን ግዛት ተከፋፍለዉ ትንንሽ ነገስታት ሆነዉ ለአንዲት ኢትዮጵያ መፈጠር እንቅፋት የሆኑን መሳፍንቶች በጦር መደምሰሳቸዉ፣ የዘመኑን ቅጣት መቅጣታቸዉ በዚህ ዘመን ላይ ቆመን ስህተት ነበር፣ትክክል ነበር እያሉ በዚህኛዉ ዘመን የእሴት ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ለመተንተን እና ቴዎድሮስን ጨካኝ መሪ ብሎ ለመፈረጅ መነሳት መሰረታዊ የታሪክ ህጸጽን ያነገበ አካሄድ ነዉ። የቴዎድሮስን አንዲት ኢትዮጵያን የመፍጠር ዉለታና ታላቅ ራዕይ ገደል ለመስደድ  በዘመኑ ቅቡል የነበረዉን ስትራቴጅ ለመተቸትና በዚያ ስትራቴጅም ሰበብ የተነሳ የመሪዎችን ተክል ሰብዕና ለማቀጨጭ መስራት የሀገር ህልዉና ምነዉ ፈርሶ ተደርምሶ ከሚሉ ሰዎች ብቻ ሊደመጥ የሚገባዉ ትንታኔ እንጅ ኢትዮጵያን ከሚወዱ ወገኖች ግን ፈፅሞ ሊደመጥ የሚገባዉ ጉዳይ አይደለም፡፡

ወይም ደግሞ የአንድን ንጉስ የተለዬ ባህሪያት በመንቀስና በማዉጣት መላዉ የሀገሪቱ ታሪክና ጉዞን ሁሉ በዚያ ማዕቀፍ በመሸበብ ስለአንድ ሀገር፤ ስለአንድ ማህበረሰብ ጠቅላላ ድምዳሜም መስጠት ችኩልነት ነዉ፡፡ የአፄ ቴዎድሮስን ሀገር አንድ የማድረግ ስልትና ስትራቴጅ በመጥቀስ የኢትዮጵያን ባህላዊ የስልጣን እሴት በአንድ ኩነት ዉስጥ ቀንብቦ ለማሳዬትና አፄ ቴዎድሮስንም የዚህ ዘመን የአንባገነንነት እሴት ማሳለጫ አድርጎ ለማሳዬት መትጋት የአገሪቱን ታሪክ በጎረዶዉ መረዳት ወይም በግዴለሽነት ለራስ ትንታኔ የሚበጅን ጉዳይ ነቅሶ የማዉጣት ብልጠት ነዉ፡፡ ለምን?

በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ነገስታትና ሃያላን ሰዎች የእርስ በእርስ መጠፋፋትን ለማስቀረት ሲሉ ከአንደኛዉ ወገን ወደሌላኛዉ ወገን ስልጣንን በድርድር ያሸጋገሩበት ወቅት ነበር። ይሄም የድርድር ስልትና ጥበብ ሀያሉ ስልጣኑን ይዞ እንዲቀጥል ሲያስችለዉ ደካማዉም ቢያንስ በሃያሉ ህልዉናዉ ሳይደመሰስ የህልዉና ዋስትና አግኝቶ እንዲቀጥል እድልን ሰጥቶታል። ለምሳሌም የሰለሞናዉያንን እና የዛግዌ ነገስታትን ዉልና ድርድር ማስታወሱ በቂ ነዉ። ይህ የኢትዮጵያ ታሪክ አንዱ ገጽታና የባህላዊ የስልጣን ስር ነዉ። ሌላም ታሪካዊ ክስተት መዞ ማምጣት ይቻላል። አጼ ዮሐንስና ዐጼ ሚኒሊክ በስልጣን ባልተግባቡ ጊዜና ጦር ለመማዘዝ በተቃረቡ ጊዜ ሊመዘዝ የነበረዉ ጦር በድርድር ወደ አፎቱ እንዲገባ ተደርጓል። የሁለቱ ንጉሶች ድርድር ሁለት ሶስት ጊዜ እየተደረገ የቀረዉ ጦርነትና እርስ በእርሳቸዉ ሳይጠፋፉ የሃይል ሚዛናቸዉን ሁለቱም ጠብቀዉ የተጓዙበት የድርድር ታሪክም በራሱ አንዱ የኢትዮጵያ የታሪክ ገፅታና ባህላዊ የስልጣን እሴት ነዉ፡፡

ሆኖም አንዳንድ ጸሃፊዎች ይሄንም የታሪክ ክፍል ማንሳት አይፈልጉም ። ምክንያቱም ያለፈዉን የኢትዮጵያ ታሪክ ለመኮነን ስለማያመቻቸዉ ነዉ። ሌሎች ደግሞ ይሄን የሃይለኞች ድርድርና ያለመጠፋፋት ጥበብ ከተንኮልና ከሸር ጋር ሊያያይዙት እንቶፍ እንቶፍ ሲሉ ይስተዋላሉ። ቁልጭ ያለዉ ሚስጥርና እዉነት ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ አንዳንድ ጊዜ ለስልጣን የሚሻኮቱ ሀያላን ጦረኞች የሃይል ሚዛናቸዉን እያመዛዘኑ ወደ አዉዳሚና ሁል አቀፍ ጦርነት ከመግባት ይልቅ በድርድር የስልጣን ሽግግር ያደርጉ እንደነበረና ይሄም አንዱ የታሪካችን አካል መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል እንጅ ሌላ ትርጉም አሰሳ መሄድ አስፈላጊ እንዳልሆነ ነዉ። ሆኖም በዘመነ መሳፍንት ጊዜ በነበረዉ ቅጥ ያጣ ሁኔታ  ይህ የኢትዮጵያ ባህላዊ ድርድር ድምጥማጡ ጠፍቶ  አገሪቱም እራሱዋ ድምጥማጡዋ ጠፍቶ ነበርና አፄ ቴዎድሮስ ከባላንጣዎቻቸዉ ጋር ያለቸዉን ልዩነት በድርድር ስልት ማጥበብ አልቻሉም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳና ድርድርን የስትራቴጅያቸዉ አካል ማድረግ ባለመቻላቸዉ አፄ ቴዎድሮስ የሚወቀሱበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡

ሌላም የታሪክ ክፍል አለን። ይሄዉም ነገስታት በራሳቸዉ ፈቃድ በመነሳት ስልጣን በመልቀቅ ሌላ የሚሆናችሁን ተኩ እኔ እግዚአብሄርን ማገልገል እፈልጋለሁ እያሉ ከሃላፊነት በራሳቸዉ ፈቃድ የሚነሱበት የታሪክ ክስተቶችንም ያስመዘገብን ህዝብ ነዉ። እንግዲህ የኢትዮጵያን ባህላዊና ታሪካዊ የስልጣን እሴት ለማዉራት አንዱን ክስተት ብቻ መዞ  ፤ የአጤ ቴዎድሮስንም አገር አንድ የማድረግ ስልት  እንደማሳያ ነቅሶ ለወቀሳ ብቻ መንደርደርና በዚህ የታሪካዊና ባህላዊ ትንታኔ ላይ ተመስርቶ ባህላዊ የዘመኑን ፖለቲካም ለመተንተን መነሳሳት በራሱ በርካት እጸጾችን አስከትሎ መንጓተቱ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። አንዱና ዋናዉ ስህተቱ የአፄ ቴዎድሮስን አገራዊ  አስተዋፅኦ አኮስምኖ ዛሬ ያለዉ ትዉልድ ለሰራቸዉና ለሚሰራቸዉ ስህተቶች ምክንያት/ሰበብ ፍለጋ ወደ አፄ ቴዎድሮስ ድርጊት ለመሻገር ያለ ተጠይቃዊ መጨበጫ በመሳብ ለአሁኑን ዘመን ደንበርባራ ስህተት ባህላዊ እሴታችን ተጠያቂነት አለበት በሚል ማምለጫ ለመዘጋት መሞከር ነዉ፡፡

በአጠቃላይ አፄ ቴዎድሮስን በሚዛን ላይ አዉጥተን ሀገራዊ ትዊፊታቸዉን ልንሰፍረዉና ልንለካዉ የምንችለዉ በራዕያቸዉና ከራዕያቸዉ በተወለደዉ ሀገራዊ አሴት ነዉ ወይስ ራዕያቸዉን እዉን ለማድረግ በተከተሉት ስትራቴጅና ስልት ነዉ? ደግሞስ ስልትና ስትራቴጅአቸዉ ላይ እናተኩር ብለን ብንነሳ የተሻለ ስልትና ስትራቴጅ አማራጭ እያላቸዉ ያልመረጡት ምርጫ ምን ነበር?

የአዉሮፓ ሀገራትን በፊዉዳል ዘመን ወቅት ያዋሃዱ መሪዎች የተከተሉት ሀገር የማዋሃድ ስልት ምን ነበር? ከቴዎድሮስ የተለዬ ነገር ነበረዉ? በዚህም ተባለ በዚያ አንድ ነገር መገምገም ያለበት እና እዉነታዉ ተጨምቆ መዉጣት ያለበት በሁለት መሰረቶች ላይ በመቆም ነዉ፡፡ አንደኛዉ መሰረት አጠቃላይ አዉነቶች ላይ በመመርኮዝ/Avoiding Exceptions/ ሲሆን ሁለተኛዉ መሰረት ደግሞ እመሰረታዊዉ ጭብጥ ላይ በመመርኮዝ የኩነቱን አጠቃላይና ልዩ ማዕቀፎች መርምሮ በማዉጣት መሆን አለበት፡፡ በዚህ መሰረትም ነገሩን ቀረብ ብለን ከመረመርንዉ አጤ ቴዎድሮስ የነበሩበት አጠቃላይ ማዕቀፍና ልዩ ኩነቶች ብሎም የፊዉዳል ስርአት መሰረታዊ ባህሪያት ጦርነት ፤ ጉልበት፤ እንቢተኛን ለመግራት ብሎም እጅግ ያስቸገረዉን ደግሞ አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ወደ ማእከላዊ ግዛት መቀላቀል ዋናዉ የሀገር አንድነት እዉን ማድረጊያ ሰልት / ስትራቴጂ ሆኖ ይወጣል፡፡

እንኩዋን በዚያ ዘመን በዚህኛዉም ዘመን የቃላት መቀባባት ፤ የፅንሰ ሀሳብ መለጠጠ ብሎም የቀለታማዉን ጉልበት አዞሪት የአጨዋወት ስልት መቀያዬር ካልሆነ በቀር ዋንኛዉ የሀገራት አንድነትና ህልዉና ማስጠበቂያም ሆነ የልዕለ ሀያልነታቸዉ ማሳለጫ ያዉ ጦርነት እና ጉልበት ሆኖ ጥርሱን አግጦና አይኑን አጉረጥርጦ ከወጣ ብሁዋላ ዲሞክራሲያዊ ወይም ፍትሃዊ ጦርነት/ተመጣጣኝ ጉልበት አጠቃቀም / በሚል ስነ አመክንዮ ተጀቡኖና ተዉቦ ይመጣል እንጂ ጥሬ ሀቁ ያዉ የሀገር አንድነት ጉዳይ ሲነሳ ጉልበትና ጦር መክፈቻና መዝጊያዉ ቁልፉ ነዉ፡፡

እናም ከታሪካችን በጥቂቱም ቢሆን ተቆንጥሮ የሚወሰድና ለዚህ ዘመን ግብአት ሊሆን የሚችል አዎንታዊ ቁምነገር አናጣም የምንል ኢትዮጵያዉያን ወገኖች ከቀደመ ታሪካችን መልካም እሴቶቸን ለማደብዘዝ ተፋጥነን ወደ አጉዋጉል ድምዳሜ ላለመሄድ ከሚከተሉት ሁኔታዎች መታቀብ ጥሩ ነዉ፤

ታሪክን ከፖለቲካ ጋር አሳክሮ ለመተንተን መግደርደር፤ የሁለት ሀገሮችን የማይዛመድ ታሪክ በግድ ይዛመዳል በማለት ጥልቅና ቁልፍ የሆነችዉን የልዩነት ክር ፈልፍሎ ሳያወጡ ተመሳሳይ ታሪክ የሚመስሉ ጉዳዮችን በመጠቃቀስ ታሪክን ከታሪክ ጋር አሳክሮ ለመተንተን መሞከር እንዲሁም በሀገር ፍቅር ከመቃጠል የተነሳ ብሎም በሀገራችን ድህነትና ያልተሳካ የብልፅግና ጉዞ ምክያት ተስፋ በመቁረጥ የቀደመዉን ሁሉ የመካድ/የመንቀፍ አካሄድን መግታት ተገቢ ነዉ፡፡ ቁሳዊ ብልፅግና መልካም ስርዐት ብሎም ጠቢባን መሪዎች በምድሪቱ ሲነሱ በአጭር ጊዜ እዉን የሚሆን ክስተት ሲሆን በጋራ ሀገራዊ መሰረት ላይ የቆሙ የጋራ ሀገራዊ እሴቶች ግን በክህደትም ይሁን በነቀፌታ ከኮሰመኑ፤ ከጠፉና ወደ መቀመቅ ወርደዉ ከተቀበሩ ቁሳዊ ብልፅግናዉን አፋጥኖ ለመራመድ የጋራ መሰረትና ስር ስለማይኖር ሀገር ብልፅግናዉ ቀርቶበት እንደሃገር መቆሙ ራሱ ፈተና ይሆንበታልና ጥንቃቄ ቢደረግበት መልካም ነዉ፡፡ ያለዉን የማያዉቅ ሀገርና ህዝብ የሌለዉን ከምን አምጥቶ፤ እምን ላይ አቁሞ የዳበረ ማንነትን መፍጠር ይችላል?

በተለይም አክሱማዊነትን የማያዉቅ አክሱማዊ በሚለዉ ድንቅ ትንታኔዉ ለቀደመ ኢትዮጵያዊነት ታላቅ አክብሮትና እዉቀት እንዳለዉ ያስመሰከረዉ በእዉቀቱ ስዩም በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ሲደርስ በፅንፍ ላይ የቆመ አቁዋም በመያዝ ከዚያ ዘመን ይኖር ከነበረዉ ማህበረሰብ የአጤ ቴዎድሮስ የሞራል ልዕልና ያነሰ ነበር የሚለዉን ድምዳሜዉን ማረም አለበት፡፡ እንዲሁም በርካታ ድንቅ መፅሃፍትን በመፃፍ ከማንኛዉም ምሁር በላይ የመፃኢዉን ኢትዮጵያዊ ስነልቦና በመቅረፅ ብሎም ትክክልኛ ሀገራዊ ራዕይን እንዲፈልግ ከፍተኛ የአዕምሮ ስራ የሰሩት ጉምቱዉ የእዉቀት አባት ፕሮፌሰር መስፍን የአጤ ቴዎድሮስን ሀገራዊ እሴት ከባህላዊ ኩነቶች ጋር በማዛመድ አለ አግባብ በዚህ ዘመን ላለዉ አምባገነን ስርዐት ማሳለጫና ማነጻፀሪያ ለማድረግ ያቀረቡት ትንታኔ መሰረታዊ ስህተት ስላለበት መታረም አለበት እላለሁ፡፡

ሰላም ለሁላችን